# የአብነት ትምህርት ቤቶች

*ጉት ከበደ*
*ማኅበረ ቅዱሳን*
*ገዳማትና አድባራት እና የአብነት ት/ቤቶች*
*መርጃና ማቋቋሚያ ንዑስ ክፍል*
*ስ.ቁጥር 565159*



*ጉት ከበደ የጥናት ወረቀታቸውን ሲያቀርቡ*

1. **መግቢያ**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ካበረከተችው የእምነት እና የሥራ ውጤት አንዱ ዛሬ በዓለማችን ላይ የራሳቸው ፊደላት ካላቸው ጥቂት ሀገሮች ውስጥ ብቸኛዋ የአፍሪካ ሀገር እንድትሆን ማድረጓ ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ በእነዚህ ቁጥር እና ፊደላት የመጀመሪያ ተጠቃሚዎቹ ደግሞ የቆሎ /የአብነት/ ትምህርት ቤቶች ናቸው።

ቀለም ቢበጠብጥ፣ ብራና ቢፋቅ፣ መጽሐፍ ቢጻፍ፣ በወርቅ ቢለበጥ፣ በእንጨት ገበታ ላይ ቅዱሳ ቢሳሉ፣ ካህኑ፣ መሪጌታው፣ የኔታ፣ ሊቀ ጳጳሱ፣ ፓትርያርኩ ሁሉም በአጠቃላይ ከቆሎ /በአብነት/ ትምህርት ቤት ውጤት ናቸው።

የዘመናዊ ትምህርት ወደ ሀገራችን ከመግባቱ በፊት ቀደምትነት እንዲሁም ለዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት መሠረትነት ያላቸው እነዚህ የዛሬዎቹ የአብነት ትምህርት ቤቶች መሆናቸው የማይካድ ሀቅ ነው። የቆሎ ተማሪ ከተባለ ብዙዎቻችን በአእምሮአችን ውስጥ የተሳሉ ነገሮች አሉን። ይኸውም የቆሎ ተማሪ ማለት የገ ለምኖ ካልበላ፣ ውኃ ካልነካሰው፣ እከክ ካልያዘው ብቻ በደፈናው ካልተቸገረ ትምህርት እንደማይገባው እንደሆነ ነው። ይህንንም ለረጅም ጊዜ የቆሎ ተማሪዎችም፣ ኅብረተሰቡም አምኖበት የሚሠራበት ነበር። ዛሬስ? ይህን አባባል ተማሪውም

ኅብረተሰቡም ይቀበለዋል? እነዚህ የአብነት ትምህርት ቤቶች ዛሬ በምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ?

ዛሬ እየመነመኑ እና እየተዘጉ ለመጡት የአብነት /የቆሎ/ ትምህርት ቤቶች ዋና መንስኤዎች ምንድናቸው የሚለውንም ማየት አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም የዛሬ የአብነት ትምህርት ቤቶቻችን የነገው ተተኪ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት አባቶች ማፍሪያ መድረኮቻችን ናቸውና።

## 1.1 የጥናቱ ዓላማ

በአሁኑ ወቅት እየተዳከሙ የመጡትን የአብነት ትምህርት ቤቶች ምክንያታቸው ምን እንደሆነ በማጥናት ጠቃሚ መፍትሔዎችን ከመሰንዘር፣ ከዚህ በተጨማሪ ለሌሎች ጥናቶች መነሻ እንዲሆን እና በርዕሱ ዙሪያ ላለው ችግር ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መፍትሔ ለመፈለግ ነው።

## 1.2 መላምት

የአብነት ት/ቤቶች ጥናት በነበሩበት ሁኔታ ስላሉ ወይንም አሁን ካለው ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጋር አብረው ስላልሄዱ እየመነመኑ እና እየተዘጉ ይገኛሉ።

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

የአብነት ት/ቤቶች ያለባቸውን ችግሮች ለማየት እና መፍትሔ ለማፈላለግ

## 1.4 የጥናቱ ዘዴ

ይህን ጥናት በሰድስት ገዳማት በሚገኙ 15 የአብነት ት/ቤቶች ውስጥ በመማር ላይ ላሉ 166 ተማሪዎች የቡድን ውይይት /focus group discussion/ በማድረግ ለ15 መምህራን እና ከገዳማቱ አስተዳዳሪዎች ጋር መጠይቆችን በመጠየቅ እና የመስክ ምልከታ በማድረግ እንዲሁም የተለያዩ ጽሑፎችን በማንበብ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሞክሯል።

## 2. በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች እና የሚወስድባቸው ዘመን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የዕውቀት ምንጭ ናት። ዘመናዊ ትምህርት ወደ ሀገራችን ሳይገባ ቤተክርስቲያን የአብነት /የቆሎ/ ትምህርትን በሥርዓቱ ከፋፍላ ለተማሪዎችም ደረጃ አውጥታ ስታስተምር ኖራለች፣ አሁንም በማስተማር ላይ ትገኛለች። በዚህ የትምህርት ሕይወት ውስጥ የቤተክርስቲያን አባቶች ብቻ ሳይሆኑ በግብርናውም፣ በንግድም እንዲሁም በዘመናዊ ትምህርት ውስጥ የገቡ ሁሉ የሚያልፉበት፣ ያለፉበት ነበር። ዛሬም እያለፉበት ይገኛል። ስለዚህ ለዚህች ሀገር ይህች ቤተክርስቲያን እጅግ ብዙ ነገሮችን አበርክታለች። ከነዚህም ውስጥ፣

ሀ. ሙሉ ትምህርት

ለ. ፍፁም ቋንቋ ከነፊደሉ

ሐ. ሥነ ጽሑፍ ከነሰዋሰዉ፣ ከነሙያው

መ. ኪነ ጥበብ በየዓይነቱ

ሠ. ሥነ ጥበብ በየመልኩ

ረ. ታሪካዊና ጥንታዊ ቅርስ

ሰ. እምነት ከነፍልስፍናው

ሸ. ነፃነት ከነክብሩ

ቀ. አንድነት ከነጀግንነቱ

በ. አገር ከነድንበሩ

ተ. ስም ከነምልክቱ ከነትርጉሙ /አባ ጎርጎርዮስ፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ 1974 ፣ ገጽ 9/

www.ethiopianorthodox.org

አሁንም ቢሆን ትውልዱ ጀግንነትን፣ አገር ወዳድነትን ለታሪክ፣ ለባሕልና ለሃይማኖት ተቆርቋሪነትን ይዞ እንዲያድግ በማስተማርና በማበረታታት ቤተክርስቲያን የበኩሏ ድርሻ አላት። ጥንታዊት፣ ታሪካዊት እና ብሔራዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርቱን በሦስት ታላላቅ ክፍሎች ከፍላ እያስተማረች ትገኛለች። እነርሱም፣

1. ለጀማሪዎች /የወጣንያን/
2. ለማስከላቺያን /መለስተኛ ዕውቀት ላላቸው/
3. ለምሁራን

## 2.1 ለጀማሪዎች /ለወጣንያን/

ለጀማሪዎች ወይንም ለወጣንያን የሚሰጠው ትምህርት ንባብ ቤት በመባል ይታወቃል። በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጠው በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች ሲሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ልጆች አራት ዓመት ከሞላቸው በኋላ የሚጀምሩት ነው። ይህ ለጀማሪዎች የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት ሦስት ክፍሎች አሉት።

ሀ. ፊደል ት/ቤት

ለ. ፊደል ሐዋርያ

ሐ. ግብረ ሐዋርያ /ንባብ ሐዋርያ/

### ሀ. ፊደል ት/ቤት /የፊደል ሥርዓተ ትምህርት/

በዚህ የመቀሰለ ሕፃናት ት/ቤት ለቋንቋው መሠረት የሆኑ ፊደላት በጥንቃቄ ይሰጣሉ። እያንዳንዱ ፊደል ሰባት የተለያዩ ቅርፆች /አነጋገሪ ቅጥያዎች/ ያሉት ሲሆን ይህ ክፍል እነዚህን ለይቶ ለማወቅ ያስችላል። ከዚሁ ጋር የአቡጊዳ ፊደላትን የአኃዝን /የሒሣብን/ ትምህርት ከፊደሉ ጋር አብረው በመዝለቅ የቁጥርን መልክና ቅርጽ እንዲሁም የግእዝ አቆጣጠርን ያጠናሉ።

### ለ. ፊደል ሐዋርያ

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚማሩት /ሕፃናቱ/ የፊደልን ትምህርት በሚገባ አጠናቀው የመጡ ሲሆን እዚህ የሚማሩት «መልእክተ ዮሐንስ ሐዋርያ ወልደ ዘብዴዎስ» ብለው ስለሃይማኖት ጥልቅ ምሥጢር የያዘውን የሐዋርያው የቅዱስ የሐንስን መልእክት /ምዕ1÷1/ ፊደላቱን በሚገባ ካወቁ በኋላ በአንደኛው ደረጃ ግእዙን ይማሉ። ይህም ማለት ከቁጥር ለቀቅ ባለ መልኩ ሁለቱን ፊደላት አንድ ላይ አድርገው ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራ፤ ከላይ ወደታች፣ ከታች ወደ ላይ፣ በመስቀልያ ይመላለሱታል። በሁለተኛ ደረጃ ውርድ /ንዑስ/ ንባቡን በዕለተ ስቅለት ግብረ ሕማማት በሚነበብበት የኃዘን መልክ ባለው ዜማ ያነባሉ፣ በሶስተኛ ደረጃ ቁም /ዓቢይ/ ንባቡን ያለ ችግር በትክክል ያነባሉ። ከዚህ በኋላ ተማሪዎች ከፊደል ቆጠራ እንደወጡ ተደርገው ይቆጠራሉ።

### ሐ. ግብረ ሐዋርያ /ንባብ ሐዋርያ/

በዚህ የትምህርት ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች ሳይቆጠቡና ሳያግዙ ያገኙትን መጽሐፍ እንደተረበላቸው በቀጥታ ተነሺውንና ወዳቂውን ሩቅና ቅርቡን ወንዱንና ሴቱን ነጠላውንና ብዙውን ለይተው ዘርፍና ባለቤቱን ያነባሉ። በቤተ ክርስቲያን የተወሰኑትን ለንባብ አስቸጋሪ መስለው የተገመቱት መጻሕፍት መጽሐፈ ግንዘት፣ አርጋኖን፣ መቅድምና ተአምረ ማርያም፣ ተአምረ ኢየሱስ፣ ውዳሴ አምላክና መጽሐፈ አርድእት የመሳሰሉት ናቸው። በቅዳሴ ጊዜም በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ሃይማኖተ አበው ከቅዳሴ በኋላም ስንክሳርን በአትሮኑስ ላይ ዘርግተው ያነብባሉ።

ከዚህም ሌላ በጥንቱ ሥርዓተ ትምህርት ላይ ለልጆች የግብረ ገብ ትምህርት ከፍተኛ ቦታ ነበረው። ልጆች በግብረ ገብ ታንፀው እንዲያድጉና ትህትና እንዲሠሩ፣ ታላላቆችን እንዲያከብሩ የተለየ ትምህርት ይሰጣቸዋል። በተቻለ መጠንም ልጆች መጻሕፍተ ሰሎሞንን እንዲያነቡና

www.ethiopianorthodox.org

በውስጡም ያለውን ምሥጢር እንዲያውቁ ያደርጓቸዋል:: ከሕግጋትም ውስጥ የግብረ ገብነትን እና የእምነት አንቀጽ ያለበትን ያስጠኑአቸዋል::

2.2 ለማዕከላውያን /መለስተኛ ዕውቀት ላላቸው/

ለማዕከላውያን ወይንም መለስተኛ ዕውቀት ላላቸው የሚሰጠው ትምህርት በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መከናወን የሚገባቸው የትምህርት ዓይነቶች ናቸው:: እነዚህም

2.2.1 ዜማ

2.2.2 የቅኔ ትምህርት ናቸው

2.2.1 ዜማ ቤት

ዜማ ማለት የምስጋና መዝሙር ስልት ያለው ጩኸት፣ የንዋየ ማኅሌት፣ የደስታ ድምጽ ማለት ነው:: ደራሲው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እንዚራ ቅዱስ ያሬድ ነው:: የዜማው ስልት በሦስት መሠረታውያን መደቦች ይጠቃለላል:: እነሱም ግእዝ፣ እዝል እና አራራይ በመባል ይታወቃሉ:: በዜማው ሥርዓት ውስጥም ዋና ዋና ምልክቶቹ ድፋት፣ ይዘት፣ ሂደት፣ ጭረት፣ ቅናት፣ ቁርጥ፣ ርክርክ፣ ደረት፣ ድርስ፣ አንብር ናቸው::

የዜማ ቤት ጸዋትዎ ዜማን /ቅዳሴን፣ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ እና መዋስዕት/ የቅዱስ ያሬድን ድርሰት ሁሉንም ያጠቃልላል:: እነዚህ ትምህርቶች ብዙ ጊዜ የጩኸት ትምህርት በመባልም ይታወቃሉ:: የቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት በቁጥር አምስት ሲሆኑ እነርሱም፡- ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬና መዋሥዕት ይባላሉ::

ሀ. ድጓ

በትርጉሙ ዜማ መዝሙረ ኃዘን፣ ሙሾ፣ ረቂቅ ማለት ሲሆን በታላላቅ በዓላትና በሰንበተ ክርስቲያን የሚደርሱትን የዓመቱን መዝሙራት አጠቃልሎ የያዘ የዜማ መድብል /ምንጭ/ ነው:: ስለዚህ ሌሎች የዜማ መጻሕፍት ሁሉ ከዋናው ምንጭ ከድጓ የተቀዱ ናቸው::

ድርሰቱ በጥራቱ ብቻ ሳይሆን በኃይለ ቃሉ ታላቅ እንደመሆኑ ለዝማሬ ይመች ዘንድ በአራት ወንጌላት ምሳሌ በአራት አርእስት ተከፍሏል:: እነርሱም ዮሐንስ፣ አስተምህሮ፣ ጾመ ድጓና ፋሲካ ይባላሉ:: እንድም በአራቱ እንስሳት ኪሩቤል አምሳል ቁም ዜማ ፣ ዝማሜ፣ ድፋትና መረግድ የተባሉ የዜማ ስልቶች አሉት::

የታወቀው የድጓ ማድረሻ ጊዜ አራት ዓመት ሲሆን አንዳንድ ፈጣን ተማሪዎች ግን ከዚህም በፊት ፈጽመው ይሄዳሉ:: እስከ ስባት ዓመትና ከዚያም በላይ የሚቆዩ አሉ:: የዜማ ምልክቶችን ከጠረፍ እስከ ጠረፍ በቃል አጥንቶ ጽሮ አመልክቶ ጥሩ የድጓ መምህር ለመሆን ከ10-15 ዓመታት ሊወስድ ይችላል:: ስለድጓ ሲነሳ የማይታለፈው ድጓ ዛሬ አንድ ዓይነት ሆኖ የዜማው ስልት /ቃና/ በአምስት ይትበሃል ይነገራል:: እነርሱም፣

1. የቤተልሔም የዜማ ልክ
2. የአጫብር የዜማ ልክ
3. የቆሚ /ዋድላ/ የዜማ ልክ
4. የተጉለቴ የዜማ ልክ
5. የወንጪሬ የዜማ ልክ ናቸው::

ለ. ጾመ ድጓ

ከድጓው አንደኛው ክፍል ነው:: ይህን ስያሜ ያገኘበት ምክንያትም በዐቢይ ጾም የሚዘመር ለጾም ጊዜ አገልግሎት የተቀመረ በመሆኑ ነው:: ጾመ ድጓ ለብቻው ወንበር ባይኖረውም ከምዕራፍ ጋር ለጀማሪዎች ይሰጣል:: ጾመ ድጓን ደህና አድርጎ ለማጠናቀቅ ከአንድ ዓመት ያ ላነሰ ጊዜ ይወስዳል::

www.ethiopianorthodox.org

ሐ. ምዕራፍ

በዐቢይ ጾም የሚደርስ በሰንበትና በክብረ በዓላትም ከዋዜማው ጀምሮ የጸሎት የምስጋናና የዜማ ሥርዓት የሚከናወንበት ነው። ምዕራፍ በቀጥተኛ ትርጉሙ ማረፊያ ማሳረፊያ ማለት ሲሆን በዜማ ቤት ደግሞ በመላ ሰላም ለኪ ብሎ ጀምሮ የጾም ምዕራፍ እስኪፈጸም ድረስ ያለው ትምህርት ሁሉ ምዕራፍ በመባል በሁለት ይከፈላል። የምዕራፍ ትምህርት ሁለት ዓመት ይወስዳል። ይኸውም ተማሪው ትጉህ የሆነ እንደሆነ ነው። ምዕራፍንና ጾመ ድጓን የሚያስተምር መምህር መጋቤ ስብሐት ይባላል።

መ. ዝማሬ መዋሥዕት

ዝማሬ ማለት ምስጋና ሲሆን የሥጋ ወደሙ ሥነ ሥርዓት ከተከናወነ በኋላ በምሥጢረ ቁርባን ከብር የሚዘመር ኅብስት፣ ድምፅ፣ መንፈስ፣ አኮቴትና ምሥጢር የተባሉ አምስት ክፍሎችን የያዘ ድርሰት ነው።

መዋስዕት ማለት ደግሞ እንደ ጸሉተ ግንዘትና ፍትሐት የሚጸለይ ሲሆን በነግህ በሥርዓተ አርያም ይቀርባል ። አንድ ተማሪ አስቀድሞ በዜማ የገፋ/ዘረ ደፋር/ ከሆነ በሁለት ዓመት ዝማሬ መዋሥዕት አውቆ በስድስተኛ ዓመት እስመስከዮ መምህር ሲሆን ይችላል።

ሠ. አቋቋም

የመቆም ሥነ ሥርዓት ወይንም ማኅሌት በሚቆምበት ጊዜ የአገልግሎቱን ልክና መልክ የዜማውን ስልትና ሥነ ሥርዓት የሚገልጥ ነው። ቅዱስ ያሬድ ከጽናጽል ከከበሮ ና ከመቋሚያ አህምዶና አዋድዶ እንደ ጀመረው የሚነገር ሲሆን በአሁኑ ወቅት የሚታወቁት የአቋቋም ቤቶች አራት ናቸው። እነዚህም ሀገ በመለወጥና አንዳንድ ይትበሃል በማሻሻል የመጡ ናቸው። እነርሱም

1 የላይ ቤት- ጎንደር ከጃን ተክል ዋርካ በላይ የሚገኙ አቢያተ ክርስቲያናት የሚከተሉት ሊሆኑ መንገድ አውጥቶ በለቀቃ የሚሄድ ነው።
2 የታች ቤት- ጎንደር ከጃን ተክል ዋርካ በታች የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የሚከተሉት ሲሆኑ ጥንታውያን ማለትም ምልክቱን ተከትለው የሚሄዱ ናቸው።
3 የጎንጂ- የጎጃም ሳንኪ ጊዮርጊስ ደግሞ በቁም የሚዘመር ነው።
4 የተክሌ አቋቋም- አለቃ ገብረሃና ገብረማርያም ልጃቸው ለአለቃ ተክሌ ገ/ሃና ያስተማሩትና ምስክሩ በደብረ ታቦረ ኢየሱስ/ በደቡብ ጎንደር ደብረ ታቦር ከተማ/የሚገኙት ናቸው። የተክሌ አቋቋም ስዝማሜ /ለዘንግ/ የጎንደር አቋቋም ደግሞ ለጸናጽል የሚፈለግ ነው።

የቅዳሴ ትምህርት

ከአምስቱ የቅዱስ ያሬድ ድርሰት በተጨማሪ የቅዳሴ ትምህርት በዜማ ቤት ውስጥ የሚገኝ ነው። ግብረ ዲቁናን፣ ሰዓታቱን፣ መዝገብ ቅዳሴውን /የ14ቱን ቅዳሴያት ዜማ/ እና አንቀፀ ቅዳሴን የሚያካትት የቅዳሴ ትምህርት ነው። መዝሙሀ ቅዳሴ የተባለበት ምክንያት በዚያ የተጻፉ ቀለሞች /በንባብ ከሚባሉት ጥቂት ክፍሎች በቀር/ በሙሉ ስለሚዜሙ ነው። አንቀጸ ቅዳሴ ከመዝገበ ቅዳሴ እስከ ኪዳን ተጠጣጥቶ የተጻፈ ርክርክና ስረይ የበዛበት እንዲሁም ድርብ ዜማ ያለበት ለተማሪ አስቸጋሪ መስሎ የሚታይ ነው። ይህን የተማረና ጽፎ የያዘ ቅዳሴ ሀወቀ ይባላል። መምህርም ሆኖ ሊያስተምር ይችላል።

የ14ቱ ቅዳሴያት መጻሕፍት ደራሲዎች ልዩ ልዩ ሊቃውንት ሲሆኑ ዜማውን ያቀናበረው

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ያሬድ ነው፡፡ የቅዳሴ ትምህርት በጥንት ዘመን ከነማሬ መጥምቀ መለኮት ጋር በዙር አምባ ጸርሐ አርያም ገዳም ያስተምሩት ያስመሰክሩትም ነበር፡፡ እየቆዩ ግን የቅዳሴ ምስክር ተብሎ ይነገርለት የነበረው እስከ አሁንም ድረስ የሚታወቀው በሰሜን ወሎ ዋድላ ወረዳ የሚገኘው የስሰል ኩላ ቅዱስ ሚካኤል ገዳም ነው፡፡ ቅዱስ ያሬድ በዚሁ ገዳም ለሦስት ወር እንዳስተማረበት ይነገራል፡፡

በትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን በሽሬ ወረዳ የሚገኘው የደብረ ዓባይ ሳሙኤል ገዳም የቅዳሴ ማስመስከሪያ ሲሆን የስለልኩላ ዜማ አጠር ያለና የድጓውን ዜማ ተከትሎ የሚሄድ ሲሆን የደብረ ዓባይ ግን በዛምና ረዘም ያለ ነው፡፡ አንድ ደቀ መዝሙር በጸዋትወ ዜማ የበሰለ እንደሆነ መዝገበ ቅዳሴን ተምሮ አንቀጽ ጽፎ በሁለት ዓመታት አስመስክሮ ይወጣል፡፡ በዜማ ትምህርት ያልገፋ ከሆነ ግን ከ3-4 ዓመታት ይወስድበታል፡፡ ዲያቆናትንና ቀሳውስትን ቅዳሴና ሰዓታት የሚያስጠና መምህር መጋቤ ኀሩያን ይባላል፡፡

አንድ ደቀመዝሙር በቁም ዜማ እና በአቋቋም ት/ቤት የሚያሳልፈው ዘመን አስቀድሞ እንደተገለጠው ከአስር ዓመት በላይ በመሆኑ እነዚህን ጊዜያት የሚጠቀምባቸው ግማሹን ወደ ቅኔ ት/ቤት ከመሄዱ በፊት ሲሆን ግማሹን ደግሞ ከቅኔ ት/ቤት ከተመለሰ በኋላ ነው፡፡ እስካሁን የተማራቸው የንባብና የዜማ መጻሕፍት ሁሉ በግእዝ ቋንቋ የተደረሱ በመሆናቸው እና ትርጓሜ ያላቸውን ባለማወቅ ትሬታ አይለየውም፡፡ ስለዚህ ብዙውን ጊዜ ጾመ ድጓ ብቻ ተምሮ ወደቅኔ ት/ቤት ይዛወራል፡፡

## 2.2.2 የቅኔ ትምህርት

የቅኔ ትምህርት እንደ ዜማ ትምህርት ለማዕከላውያን /መስስተኛ ዕውቀት ላላቸው/ የሚሰጥ ትምህርት ነው፡፡ የቅኔ ትምህርት ቤት የግጥም ፍልስፍና ከነአገባቡ የሚጠናበት ትምህርት ቤት ነው፡፡ ይህ ክፍል የግእዝን ቋንቋ በስፋት የሚጠናበትና ልጆች በግእዝ ትምህርት /ዘይቤ/ የሚራቀቁበት የላቀ የትምህርት ደረጃ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት መሠረት በተሰደም በክህነት ሥራ ላይ ለመሰማራት ለሚፈልጉ የቤተክርስቲያን ልጆች ጥንትም ሆነ ዛሬ ግእዝ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ግእዝ ያልተማረ ካህን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን አይጠነቅቅም፡፡ የወንጌልንም ትምህርት የረቀቀውን አጉልቶ በልሳነ ግእዝ የተሰወረውን ሀሳብ ተርጉሞ ሰምእመናን ሊያስረዱ አይችልምና ግእዝ ማወቅ ተገቢ/ግዴታ/ ነው፡፡

የቅኔ መንገዱ ብዙ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶችም የተለያዩ ናቸው፡፡ የምዕራብ ጎጃም ዞን ይልማና ዴንሳ ወረዳ በደብረ ጽላሎ አማኑኤል የሚገኘው የጎንጅ ቅኔ፣ በሰሜን ወሎ ዞን ዋድላ ወረዳ /ኮን/ የሚገኘው የዋድላ መንገድና የጎንደር መንገድ ቀደምት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የልዩነቱ መንስኤ የዘመን ብዛት የተተኪ ምእመናን መካከልም የተፈጠሩ ጠርንቶች መሆኑ ይታመናል፡፡ በዮሐንስ ገብላዊ የተመደበ የዋድሎች የቅኔ መንገድ 650 ፣ የዋሸዎች 250፣ የጎንጆች መንገድ ደግሞ 350፣ ነው፡፡ ዋሸራና ጎንጅ ይበልጥ የሚያተኩሩት በቅኔ መንገድ ሲሆን ዋድሎች ያቆዩን ደግሞ አገባቡን /ሕጉንና ደንቡን/ ነው፡፡

ተማሪው ግሥና ነባር ካጠና በኋላ ጉባኤ ቃና የተባለችውን የቅኔ ትምህርት መግቢያ እያጋጠመ ወደ መምህሩ ፊት ቀርቦ ለመንገር ይሞክራል፡፡ መምህሩም እየረመ እያስተካከለ ይረዳዋል፣ ያበረታታዋል፡፡ ከእነዚህም እያደገ ቀስ በቀስ ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ እያሰበ ቆጥሮ ለመናገር ይችላል፡፡ አንዳንድ ክብረ በዓል በሆነበትም ቀን በየቤተ ክርስቲያኑ እየሄዱ ብዙ ሊቃውንት በተሰበሰቡበት ይበል መልካም እጹብ እያሰኘ ዋዜማ፣ ሥላሴና እግዚ ሞገር የተባሉትን ሰምና ወርቅ ቅኔዎች/ታሪክና ምሳሌ/ ይቀኛል፡፡

አንድ ደቀ መዝሙር ብልህ ከሆነ በቀላል ሰምና ወርቅ መንገድ በአንድ ዓመት ቅኔ ይቀኛል፡፡ ከ2 - 3 ዓመት ቅኔ ያውቃል፡፡ ከ4 - 8 ዓመት ስመ ጥር የቅኔ መምህር ቅኔ ዘረፋና ምስክር ሊሆን ይችላል፡፡ የቅኔና የአገባብ መምህር መጋቤ ምሥጢር ይባላል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

## 3. ለምሁራን

በሦስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መከናወን የሚገባቸው የትምህርት ዓይነቶች ለምሁራን የሚሰ ሲሆን ትምህርት ቤቱም መጻሕፍት ቤት ወይንም የንባብና ትርጓሜ ቤት በመባል ይታወቃል። በመጻሕፍት ቤት የሚሠራበትና ንባብ ለማቃናት ምሥጢር ለማደላደል የሚያመቸው ይሄው የአንድምታ ትርጓሜ ስልት ነው። በዚህም አገባብን ወይንም ዘይቤን ብቻ በመጠበቅ አለያም ምሥጢሩን በመከተል ወዲያውም ደግሞ ታሪክ በመተረክ፥ ምሳሌ በመመስል፣ ሐተታ በማተት ለእያንዳንዱ ኃይለ ቃል ሞያ ሰጥተው ይተረጉማሉ፣ የተሰወረውን ገልጠው ያስረዳሉ።

ይህ ጉባኤ ቤት መጻሕፍትን አስተካክሉ ማንበብና መተርጐም መሰረተ ሐይማኖትን የክርስትናን ታሪክ የመሳሰሉትን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንና የክርስትናን እምነት ጠንቅቆ ለማወቅ የሚያስችል ከፍተኛ የምርምር ተቋም ነው። በተጨማሪም ምሁራኑ ሌሎችንም የትምህርት ዓይነቶች ማለትም ዜማ፣ ቅኔ...... የመሳሰሉትን በሦስተኛው የትምህርት ተቋም ተምረው በሊቅነት በማዕረግ አስመስክረው ይወጣሉ። ለምሳሌ መዝሙረ ዳዊትን ወጣንያን በንባብ፣ መለስተኛ ዕውቀት ያላቸው በዜማ፣ ምሁራን በትርጓሜ ይማሩታል።

አንድ ተማሪ ከቅኔ ትምህርት ቤት ወጥቶ ወደ ከፍተኛ የመጻሕፍት ትርጓሜ ት/ቤት ሲገባ በዕድሜው የበሰለ በአእምሮ የተደላደለ የግእዝን ቋንቋ ጠንቅቆ ያወቀ መሆን ይገባዋል። ምክንያቱም የትርጓሜው አንድምታና ሐተታ ረዥምና ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ እርስ በእርስ ማገናዘብ፣ የተዛባውን ንባብ ማቃናትና ማስተካከል አድካሚ በመሆኑ አስተዋይ ጭንቅላት ስለሚጠይቅ ነው። የመጻሕፍት ቤት ተማሪ በጠባዩ ግብረ ገብነት ያለው የመናኝነት መልክ የሚታይበት፣ ትምህርቱን በሚገባ አጠናቅቆ በመምህርነት የሚገለጠው በእርጅና ዘመኑ ስለሆነ መጻሕፍት ቤት ሲገባ እንደ ሎጥ ሚስት ዞሮ ለማየት አይደለም የሚሉት ለዚህ ነው።

ምንጊዜም ቋንቋቸው እንዳይለወጥ ምሥጢር እንዳይፋለስ ዓይናቸው መጽሐፍ ከመመልከት አእምሮአቸው ምሥጢር ከማሽራሸር አይለይም። ሌሎች ሊቃውንት ምንም ውሉን ሲያውቁት ትንሽም ትልቅም ክርክር በመካከላቸው ከተነሳ ከመጽሐፍ መምህር እንሂድ በማለት ነገሩ ያልቅ ክርክሩም ይበርድ ነበር። ይህም ያላቸውን የላቀ አስተያየትና ጥበብ እንዲሁም ክብር ያሳያል። ይሁንና በዋና ዋና ከተሞች ሰመጥር በሆኑ አድባራትና ገዳማት ካልሆነ በቀር በየደብሩና በየገጠሩ በብዛት ከሚገኙት የዜማና የቅኔ መምህራን አንፃር የመጻሕፍት መተርጉም ቁጥር አናሳ ነው።

ይህ የመጻሕፍት ቤት ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ በአይሁድ ዘንድ የነበሩት ት/ቤቶች ሲሠራበት የኖረ ሲሆን ከሕገ ኦሪት ጋር ሊቃውንተ ኦሪት ከቀዳማዊ ሚኒልክ ጋር አብረው ወደ ሀገራቸው ከገቡ በኋላ ይዘዋቸው የመጡትን መጻሕፍተ ኦሪት/ሰምንቱ ብሔረ ኦሪት፣ መጽሐፈ ኩፋሌ፣ መጽሐፈ ሔኖክ፣ መጽሐፈ ኢዮብና እስከ ሰሎሞን ዘመን ድረስ የሚተረከውን መጽሐፈ ነገሥት ከእብራይስጥ ወደ ግእዝ በአንድምታ በመተርጐም ሲያስተምሩት ስለሚኖሩ ትርጓሜ መጻሕፍት ከዚያን ዘመን አንስቶ በኢትዮጵያ እንደተጀመረ ይታመናል። ከጊዜ በኋላም በእነ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን፣ በእነ ቅዱስ ያሬድና በመሳሰሉት አባቶች ትጋት ተስፋፍቷል።

የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት በንግግር መልክ አንድ ጊዜ ብቻ ተሰምቶ በቃል የሚጮህ ወይንም የሚነገር ትምህርት አይደለም። የመምህሩ የንግግር መልክ ማሄድ ይባላል። የጉባኤውም ዓይነት በመጽሐፍ ክፍል ብቻ ሳይሆን በሰዎች ልክ ይወሰናል። ሁልጊዜ በጧት የማይታጐሉ ጉባኤዎች አሉ። እኒህንም አልፎ አልፎ በትምህርት መልክ ይከታተሏቸዋል። ተማሪዎቹ የተማሩት በቃል እንዳይቀር በጽሑፍም ያስቀሯቸዋል።

የትርጓሜ ትምህርት ቤት አራት ጉባኤያት ሲኖሩት እነሱም፣

www.ethiopianorthodox.org

ሀ. ብሉይ ኪዳን

ለ. ሐዲስ ኪዳን

ሐ. መጻሕፍተ ሊቃውንት

መ. መጻሕፍተ መነኮሳት ናቸው:: እነዚህን ሙያዎች አጠናቀው የሚያውቁት ሊቃውንት የአራት ጉባኤ መምህር እንዲሁም አራት ዓይና የሚል የሊቅነት ስም ይሰጣቸዋል::

## ሀ. ብሉይ ኪዳን

ይህን ትምህርት ለመማር በመጀመሪያ የግእዙን ቋንቋ እና ቅኔ ማወቅ ይጠቅማል:: ይህ ከሆነ የብሉይ ኪዳንን ማለትም የሕግ፣ የታሪክ፣ የመዝሙር/የጥበብ ወይም የቅኔ እና የትንቢት መጻሕፍትን አንድ ብልህ ደቀመዝሙር በ6 ዓመታት በሚገባ ሊያጠናቅቅ እና ለመምህርነት ሊበቃ ይችላል:: እነኝህን በአራት ክፍል የተከፈሉት የብሉይ መጻሕፍት ቁጥራቸው 46 ነው:: እነዚህን አጠናቆ ያወቀ ምሁር መጋቤ ብሉይ ተብሎ ይጠራል::

## ለ. ሐዲስ ኪዳን

ሐዲስ ኪዳን በቁጥር 35 ሲሆን በጉባኤ ደረጃ ግን በሦስት ተከፍለዋል እነሱም፣

* አርባእቱ ወንጌል
* 14ቱ መልእክታት ጳውሎስ
* ግብረ ሐዋርያት
* ሰባቱ መልእክታትና የዮሐንስ ራዕይ ናቸው:: እነዚህን እያንዳንዳቸውን በዓመት ሁለት ጊዜ ያህል ይዘልቃሉ::

## ሐ. መጻሕፍተ ሊቃውንት

መጻሕፍተ ሊቃውንት ብዙትና ጥልቀት ያላቸው ከመሆናቸውም ባሻገር ንባባቸው ጠንከር ያለ በመሆኑ ይህን ትምህርት በሚገባ ለማጠናቀቅ ከ6 - 8 ዓመታት ይወስዳል:: እነዚህ መጻሕፍት እንደ ፍትሐ ነገሥት፣ መጻሕፍተ ቄርሎስ ፣ መጻሕፍተ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ሃይማኖተ አበው፣ 14ቱ መጻሕፍተ ቅዳሴያት የመሳሰሉት ናቸው::

የውዳሴ ማርያምንና የቅዳሴ ማርያምን፣ የኪዳንን፣ የትምሕርተ ኅቡአትን፣ የጸሎተ ሃይማኖትን ትርጓሜ ግን ማንኛውም የመጽሐፍ ተርጓሚ ማወቅ ይኖርበታል:: የቁጥር መጻሕፍት /አቡሻህር፣ ባህረ ሐሳብ ወይም መርሐ እውር/ ከፍተኛ ትምህርት ቢሆኑም ከአንዳንድ ሊቃውንት በቀር ሁሉም አይማሯቸውም::

## መ. መጻሕፍተ መነኮሳት

መጻሕፍተ መነኮሳት ሦስት ዓይነት ናቸው እነርሱም፣

⇒ ማር ይስሐቅ

⇒ ፊልክስዩስ

⇒ አረጋዊ መንፈሳዊ ሲሆኑ እያንዳንዳቸውን በአንድ ዓመት መፈፀም ስለሚቻል በጠቅላላው በሦስት ዓመታት ማከናወን ይቻላል:: እነዚህንም ጠንቅቆ በውቆ ለማስተማር የሚችል መምህር መጋቤ ምክር ይባላል::

## የአብነት ት/ቤቶች ያጋጠሟቸው ችግሮች

የአብነት ት/ቤቶቻችን የሚገኙት በየገዳማቱ እና አድባራቱ ነው:: እነዚህን ገዳማትና አድባራት ደግሞ ትናንት ነገሥታት በሰፈው ይኖሩት የነበሩ ናቸው:: ምክንያቱም ነገሥታት ለገዳማቱ እና አድባራቱ ሰፊ የእርሻ መሬት ሰጥተው እንዲሁም እንደነገሥታቱ የሚገባቸው ቀሮዎችን ወስነውላቸው ይኖሩ ነበር:: ገዳማትና አድባራት በነገሥታቱ ዘንድ ልዩ ቦታ ተሰጥቷቸው ነበር:: የሐሳብ ድጋፍ፣ ምክር፣ ጸሎት፣ ሲፈልጉ ሄደው የሚያማክሩት እነዚህን ገዳማትና አድባራት ነበር:: ሕዝቡም ፈሪሐ

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ያሰው ሰገዳማቱ፣ አድባራቱ ሰቆሉ ተማሪው የሚያሰቡ በአንተ ስማ ሰማርያም የሚላቸውን የተሜን ድምጽ የሚናፍቁ ተሜ ሳይመጣ ቢቀር ቅር የሚላቸው፣ መሸቶበት የመሸበት የእግዚአብሔር እንግዳ የሚሰውን ቃላት የሚናፍቃቸው ነበሩ።

ስለዚህ ተማሪዎች ከትምህርት ትምህርት ከቦታ ቦታ እያማረጡ ይማሩ ነበር። በየገዳማቱ ና አድባራቱ የትምህርት ጉባኤ ተሟልቶ እንዲሁም አንዱ የትምህርት ዓይነት ሁለት፣ ሦስትና ከዚያም በላይ እየሆነ ጉባኤዎች ተዘጋጅተው ይሰጥባቸው ነበር።

ዛሬ እንደጥንቱ ትምህርት ቤቶች ተሟልተው ጥንድ ጥንድ መሆናቸው ቀርቶ ያሉትን ትምህርት ቤቶች እንኳን ለማሟላት አጠያያቂ የሆነበት ጊዜ ነው። እንደ ትርጓሜ ያሉ ትምህርት ቤቶች በጣት የሚቆጠሩ ገዳማት ውስጥ ከመገኘታቸውም በተጨማሪ የሚማሯቸው ተማሪዎችም ያጡ እና እየተዘጉ የመጡ ትምህርት ቤቶች ናቸው። በአንፃራዊ ሁኔታ ስናያቸው ከሌሎች ት/ቤቶች አሁን ብዙ ተማሪዎች እየወሰዷቸው ያሉት ቅኔ፣ ዜማ ፣ አቋቋም እና ቅዳሴ ትምህርት ቤቶች ምንም እንኳ ከመዘጋት ቢድኑም አሁን ባሉበት ሁኔታ እንኳ ነገ ለመገኘታቸው አጠያያቂ እየሆነ ነው። ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶች፣

ሀ. በ1967 ዓ.ም በወጣው መሬት ላራሹ አዋጅ እና በ1968 በወጣው የከተማ ቦታ አዋጅ በከተማ የነበራቸው የኪራይ ቤት መወረስ፣ ደርግ የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ የነበረውን መሬት በመውረሱ ገዳማት እና አድባራትን ያለመተዳደሪያ አስቀርቷል። ይህ ደግሞ መነኮሳት እና መምህራን ይተዳደሩበት የነበረውን መሬት በማጣታቸው ገዳማት እንዲፈቱ፣ የአብነት ት/ቤቶች እንዲቀንሱ ብሎም እንዲበተኑ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ለ. ለአብነት መምህራን የሚደረገው ዝቅተኛ እንክብካቤ ለአብነት ት/ቤቶች ማሽቆልቆል ሌላው ምክንያት ነው። የአብነት ት/ቤቶች በሚገኙባቸው ቦታዎች በሙሉ ይዘ ችግር ጉልቶ ይታያል። እንደሚታወቀው የአብነት መምህራን ለቤተ ክርስቲያን ተተኪ ሊቃውንትን በማፍራት በኩል ታላቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ አባቶች ናቸው። ነገር ግን ለእነዚህ ሊቃውንት የሚደረገው እንክብካቤ እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ለረሀብና ለበሽታ፣ ለእርዛት ብሎም ለስደት የተዳረጉ ጥቂት አይደሉም። የአብነት መምህራን አስቸጋሪውን የአብነት ት/ቤት ኑሮ ተቋቁመው አስመስክረው ከወጡ በኋላ የሚከፈላቸው ክፍያ እጅግ አነስተኛ ነው። እንኳን ቤተሰባቸውን ሊያስተዳድር እነርሱንም ወር ማድረሱ ያጠራጥራል። አንዳንድ ቦታ ላይ ደግሞ ያለክፍያ በተስፋ ብቻ የሚያስተምሩ መምህራን አሉ። ይህ ሁኔታ የአብነት መምህራኑን ብቻ ሳይሆን የአብነት ተማሪዎችንም ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው።

ሐ. የአብነት ተማሪዎች መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ማሟላት አለመቻል ሌላው ችግር ነው። እንደሚታወቀው የአብነት ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ራቅ ብለው ሄደው የሚማሩ ስለሆነና ከቤተሰቦቻቸው ስለሚለዩ በትምህርት ላይ ያሉት የሚተዳደሩት በልመና ነው። ገዳማቱና ሕብረተሰቡ በጥሩ ሁኔታ ላይ በነበሩበት ዘመን የአካባቢው ሕዝብ ለተማሪዎቹ የሚያስፈልጋቸውን በመለገስ ሲተባበር ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት ግን በተለያዩ ምክንያቶች የምእመኑ መንፈሳዊ ጥንካሬ በመላላቱና ኢኮኖሚያዊ በቅሙ በመድከሙ ተማሪዎቹ እንደቀድሞው በልመና መሰረታዊ ፍላጐቶቻቸውን ሊያሟሉ አልቻሉም። ይህ ተማሪዎቹን ለስደት ስለዳረጋቸው በታላላቅ ከተሞች ውስጥ የአብነት ተማሪዎችን ሲቸገሩ ማየት የተለመደ ሆኗል። እንዲሁም ተማሪዎች መኖሪያ ቤታቸው ብዙ ጊዜ ትንንሽ ጐጆ ቢበዛ ሁለት እርምጃ ስፋት ያላት ስትሆን በውስጧም እስከ ስድስት ተማሪዎች ይኖሩባታል። ይህ ደግሞ ተማሪዎችን ለልዩ ልዩ ተላላፊ በሽታዎች ያጋልጣቸዋል። ለምሳሌ እከክ፣ የሳንባ በሽታና የመሳሰሉት የአብነት ት/ቤቶችን መጋለጥ አድክሟል።

www.ethiopianorthodox.org

ሠ. የዘመናዊ ትምህርት ቤቶች መስፋፋት የአብነት ት/ቤቶችን አዳክሟል። ይህም ሲባል የአብነት ት/ቤቶችን ከዘመናዊው ትምህርት ቤቶች ጐን ለጐን ማሳደግ ሲቻል ተረስተዋል። በዘመናዊ ትምህርት ቤት ተምረው ጥሩ ክፍያና ጥሩ ኑሮ ስለሚኖራቸው ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ አብነት ት/ቤት ከመላክ ወደ ዘመናዊ ት/ቤት መላኩን እየመረጡ ነው። ስለዚህ የአብነት ትምህርቱን የሚ ማር ተማሪ ማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ ነው።

ሡ. የማኅበረሰቡ አስተሳሰብ መቀየር ዛሬ በገዳማት እና አድባራት ስም የሚያታልሉ ሰዎች እየበዙ በመምጣታቸውና መገናኛ ብዙኃንም ይህንን አጉልተው ስለሚያሳዩት ሕብረተሰቡ ለገዳማትና አድባ ራት መርዳት ማለት ገንዘቡን እንደመስረቅ እየቆጠረውና ለገዳማዊያን የነበረው በጐ አመለካከት እየተቀየረ በመምጣቱ ገዳማት አድባራት እና የአብነት ተማሪዎችን የመርዳቱ ሂደት እየቀዘቀዘ ነው። እንዲሁም በኑሮ ውድነት ምክንያት ትናንት የነበሩትን ጥሩ ጥሩ ባሕሎች አጥንተናል። ተ ማሪዎች እንደጥንቱ በእንተ ስማ ለማርያም ብለው ለምነው ቁራሽ የሚከለክሉ አጅግ ብዙ ወቀት ያለኝን ማንሳቱ አስፈላጊ ነው። ናቸው። ዛሬ አንደ ድሮው ተሜ አይናፈቅም። በእንተ ስማ ለ ማርያም ቢል ሠርተህ አትበላም ይባላል። እሁን በአንሱ ዘንድ ተሜ በዛኔ ነው። ዲማ ቅዱስ ጊ. የርጊስ ላይ አንድ ተማሪ ባነጋገርኩበት «... ቀኑን ሙሉ ስትለምኝ ውለሽ ለምሳ የምትሆን እንኳ ላታገኝ ትችያለሽ» ብሎ ያለኝ። ሌላው ሰሚን ሸዋ ያገኘሁት ተማሪ ደግሞ ጀርባውን እያሳየኝ «በእንተ ስማ ለማርያም ብዬ ብለምን ደበደቡኝ፤ የቃለ መታወቂያህ? ውሸቱን ነው! ይህ ማነው? ከየት የመጣ ነው? እያሉ አጣደፉኝ። ወትሮስ ተማሪ በሀገሩ አይማር» አለኝ። የኑሮ መወደድ ሰውን አጨካክኖታል።

ረ. በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተደጋጋሚ የተከሰተው ድርቅ በገዳማቱና አድባራቱ ሕልውና ላይ ያስከተለው አሉታዊ ተጽእኖ የአብነት ት/ቤቶችን አዳክሟል። ምክንያቱም በሰፈሩ ሁሉም ቀዬውን እየለቀቀ ሲሄድ ገዳማቱና አድባራቱ እንዲፈቱ መነኮሳት እና ተማሪዎች እንዲበተኑ አድርጓል።

ሰ. በቤተክርስቲያን ውስጥ ማዕከላዊነትን የጠበቀ የአብነት ት/ቤት አሠራር አለመኖር፤ ለምሳሌ ከተ ማ ውስጥ የሚገኝ አንድ የቅኔ መምህርና በገጠር ገዳም የሚኖሩ የቅኔ መምህር ክፍያቸው እንድ አይደለም። ይህ ደግሞ ጥሩ ክፍያ ለማግኘት ሲባል መምህራኑ ወደ ከተማ እየተሰደዱ ነው። በገጠ ር በየገዳማቱ የሚገኙት መምህራን ወደ ከተማ ለተሻለ ክፍያ መሰደድ ደግሞ እግራቸው ሥር ቁጭ ብለው ይማሩ የነበሩትን በርካታ ተማሪዎችን እንዲበተኑ ያደርጋቸዋል።

ሸ. የምእመኑ መንፈሳዊ ሕይወት መላላቱ ሌላው ችግር ነው። ይህም ሲባል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ምእመኑ ከልጆቹ ቢያንስ አንዱ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግል ለቤተክርስቲያን በኩራቱን ይሰጥ ነበር። ተማሪዎቹም ሲማሩ፣ መምህራኑም ሲያስተምሩ የሚያስቡት ዘቀሉ ት/ቤት ተምረው የሚያገኙትን ፀጋ ፡ በረከት፣ የእግዚአብሔርን ቸርነት... ነበር። ተምረውም ሲጨርሱ እለያም አስተምረው የሚያገኙትን ክፍያ አስበው አልነበረም የሚማሩት። ለዚህ ነው አብዘኞቹ የቆሎ ተ ማሪዎች ተምረው ወደ ምናናው የሚገቡት። ዛሬ ግን እንዲህ አይደለም። ተማሪዎቹ እዚህ የአብነት ት/ቤት የገቡበትን ቀን የሚያማርሩ በወላጆቻቸው የሚያዝኑ ናቸው። አንዳንዱም እንደምንም ጥርሱን ነክሶ ጨርሶ ወደ ከተማ መግባት የሚፈልግ ነው። ይህ ደግሞ ለአብነት ት/ቤቱ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን ሕልውና አስጊ ነው።

ቀ. ሌላው ችግር የገዳማቱ አስተዳዳሪዎች በገዳማቸው ውስጥ በሚገኙት ት/ቤቶች ላይ የእኔነት ስሜት የላቸውም። ()ትምህርት ቤቱ ጨመረ መነመነ ለእነሱ ምንም ማለት አይደለም። ተማሪዎች በበሽታ ቢሰቃዩ፣ ቤቶቻቸው ብጎርፍ ቢወሰዱ፣ ቢፈርሱ ተማሪዎቻቸው መጽሐፍት ቢያጡ እነሱ ካላቸው ከፍለው መርዳት ያለባቸው አይመስላቸውም። በገዳሙ ውስጥ እንኳን ምን ያህል ተማሪ

www.ethiopianorthodox.org

እንዳሏቸው አያውቁም::

ከላይ የተዘረዘሩትን እና ሌሎች ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለገዳማት መፈታትና ለተማሪዎች ቁጥር መቀነስ ምክንያቶች ናቸው:: ስለዚህ ከላይ እንደተመለከተው በኢትዮጵያ የሚገኙ ገዳማት፣ አድባራትና የአብነት ት/ቤቶች ችግር በሀገሪቱ ሲከሰት የኖረው የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ገጽታ አለመረጋጋት ውጤት ነው::

የአብነት ት/ቤቶች ለነገው የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ማፍሪያ መሆናቸው የማይካድ ሀቅ ነው:: የአብነት ት/ቤቶቻችን ጉዳይ አነሳን ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ጉዳይ አነሳን ማለት ነው:: ምክንያቱም የቤተክርስቲያኑ መሪዎች፣ አስተባባሪዎችም ሆኑ አገልጋዮች የአብነት መምህራንና ተማሪዎች የነበሩ በመሆናቸው ነው::

ዛሬ ግን የአብነት ት/ቤቶች እንዲህ እንደ ድሮው ይቀጥሉ / እነሱ ይያዛቸው፣ ውሻ ይንከሳቸው ፣ በእንተ ስማ ለማርያም ብለው ይለምኑ/ ብሎ መተው ለነገው ትውልድና ለቤተክርስቲያን ሊቃውንት አባቶችን ማጣት ነው:: ዛሬ ያሉ የተማሪዎችና የመምህራን በተለያዩ በሽታዎች መሰቃየት ፣ ተማሪዎች በእለት ጉርስ ማጣትና ከመናፍቃን አዳራሽ ቁጭ ብለው መለመን፣ ልብስና መማሪያ መጻሕፍትን የሚረዳቸው በማጣት ከትምህርታቸው መስተጓጐል የ ማደሪያ ቤት እጥረት በማኅበረሰቡ ዘንድ ተማሪዎችን እንደ ሥራ ፈት መመልከትና በሌሎችም ችግሮች ምክንያት የአብነት ት/ቤቶች እየተዘጉና እየመነመኑ ነው:: በተለይ ለመምህራኑ የሚደረገው እንክብካቤ መቅረትና ከእጅ ወደ አፍ የማይሆን ክፍያ ተማሪዎችን ተስፋ እያስቆረጠ ትምህርቱን እንዲተውት ያደርጋቸዋል:: አናም የምናስበውን የነገ ተተኪ ሊቃውንት አባቶችን ማግኘት አጠያያቂ ነው:: ይህ ከመሆኑ በፊት ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ በተለይ ምእመናን ትኩረት መስጠት አለባቸው::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብራና ፍቃ፣ ቀለም በጥብጣ ፣ ብርዕ ቀርጻ ከፊደል ጀምሮ እጅግ ብርቅና ድንቅ የሆኑ የሃይማኖት፣ የታሪክ፣ የፍልስፍና ወዘተ መጻሕፍትን በመጻፍ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለክርስትናው ዓለም ያበረከተችው አስተዋጽኦ ወደር የማይገኝለት ነው:: ስለዚህ መንግስትም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያበረከተችውን በማገናዘብ ለቤተክርስቲያኗ ተገቢውን ድጋፍና እንክብካቤ ትኩረት መስጠት መቻል አለበት:: ሌላው ቢቀር ይህች ጥንታዊት ፣ ሐዋርያዊት እና ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የትምህርት ሚኒስቴርነቱን ኃላፊነት ይዛ ለዘመናት ኢትዮጵያን በትምህርትና በሃይ ማኖት ስትመራ መኖሯ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው::

## የመፍትሔ ሐሳቦች

1. የአብነት ት/ቤቶችን ማጠናከር የሚቻለው ት/ቤቱ የሚገኝባቸውን ገዳማቱንና አድባራቱን በማጠናከር ነው:: ይህ ሲባል ገዳማውያኑን ከተማሪዎቹ ጋር በማቀናጀት ገዳማትና አድባራትን ማልማት ነው:: ከዚያም የአብነት ተማሪዎችን ቋሚ ድጐማ እንዲያገኙ ማድረግ፣ የማደሪያ ቤቶችንና ቤተ መጻሕፍትን በማዘጋጀት እና ለተማሪ ያሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮችን ማሟላት:: ተማሪዎች ድጐማ ከገዳሙ ማግኘታቸው ለልመና ወተው የሚያጠፉትን ጊዜ በመቆጠብ በአብነት ት/ቤት የሚኖራቸውን ቆይታ ማሳጠር ይቻላል:: ስለዚህ ገዳማትና አድባራት በሚኖራቸው የልማት ሥራ ከራሳቸው አልፈው ለአካባቢው ሕብረተሰብ የሚተርፍ ገቢ ይኖራቸዋል:: በዚህም የዛሬ የአብነት ትምህርት ቤቶቻችንን እንደ ዘመናዊው ኮሌጆች በጉጉት የሚገባባቸው ማድረግ እንችላለን:: ይህን ሁሉ ማድረግ የሚቻለው ግን ገዳማቱ እና አድባራቱ ቋሚ የልማት እንቅስቃሴን በተለይ ባላቸው የሰው ኃይልና የተፈጥሮ ሀብት ጥምረት በጋራ በመስራት ነው::



www.ethiopianorthodox.org

2. ገዳማት አድባራት እና የአብነት ት/ቤቶች ማዕከላዊ በሆነ አስተዳደር የመተዳደሪያ በጀት ቢኖራቸው

3. የአብነት ትምህርትን ለአንድ ለተወሰነ ክፍል /በኀጠሪቱ የአገራችን ክፍል /ብቻ እንዳይተው ማድረግ:: ይህም የአብነት ትምህርት መማርን እንደ ኋላቀርነት እንዳይታይ ይረዳዋል:: ስለዚህ ቤተክርስቲያኗ በሷት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከኮርስ ትምህርት ጐን ለጐን የአብነት ትምህርትን መስጠት፣ ለንበት ተማሪዎች የአብነት ትምህርትን እንዲማሩ ማድረግ፣ ሠራተኛ ጉባኤያት የአብነት ትምህርት እንዲመቻችላቸው ማድረግ፣ በመረጃ መረብ የአብነት ትምህርት ቢሰጥ፣ የአብነት ትምህርት በቪዲዮና በቴፕ ካሴት በመጻሕፍት ስመሳሰሉት ቢዘጋጅ::

ከላይ የተጠቀሱት ከተመቻቹ ማንኛውም ምእመን የትም ሆኖ የአብነት ትምህርትን በማግኘት ሊማር ይችላል:: ስለዚህ ነገም እንደትላንቱ ተተኪ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት የሆኑ አባቶችን ማፍራት ቀላል ይሆናል::

## ዋቢ መጻሕፍት


1. አባ ጎርጎሪዎስ ካልዕ /ሊቀ ጳጳስ/ ፣ <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን</u>
   1974 ዓ.ም
2. ክፍያለው መርሐዊ /ቀሲስ/ <u>የቤተክርስቲያን አስተዋጽኦ ለቤተክርስቲያን ሥልጣኔ</u>፣
   አዲስ አበባ፣ 1986 ዓ.ም
3. ኪዳነማርያም ጌታሁን /መምህር/፣ <u>ጥንታዊ የቆሎ ተማሪ</u>፣ አዲስ አበባ፣ 1980 ዓ.፡
4. <u>ሐመር</u>፣ 9ኛ ዓመት ቁጥር 3፣4 እና 5 1994 ዓ.ም




www.ethiopianorthodox.org

# ማኅበረ ቅዱሳን

**ታሪክ፡-** ማኅበሩ በ1977 ዓ.ም. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በነበሩ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ተመሠረተ። ከዚያም በተጠናከረ መልክ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖቻቸው የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች እንዲሆኑ፣ የሩቅ ተመልካች የነበረውን ትውልድ ቀርቦ ማንነቱን እንዲያውቅና እናት ቤተ ክርስቲያኑን ለማገልገል እንዲችል በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያበረክት ቆይቷል። አሁንም በማበርከት ላይ ይገኛል። በ1984 ዓ.ም. በአባቶች ቡራኬ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን የሚለውን ስያሜ አግኝቶ በተጠናከረ መልክ አገልግሎቱን እንዲያበረክት ተደረገ። እስከ አሁን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ቁጥራቸው ሺህ የሚቆጠሩ አባላት የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ሥርዓትና ትውፊት በየሰንበት ት/ቤቱ እንዲማሩ በማድረግ በአባቶች ቡራኬ አስመርቋል።

**ስያሜ፡-** ነቢያት የተነበዩላት፣ ቅዱሳን ሐዋርያት ያስተማሩላትን፣ ቅዱሳን ሰማዕታት የተጋደሉላትን፣ ሥርዓቷን ዓለም ያሸነፉባትን ቀናተኛ ገዳማት የሚታወቁባትና የቅዱሳንን አማላጅነትና ክብር የሚዘክርበት በመሆኑ ማኅበረ ቅዱሳን ተብሏል።

**ዓላማ፡-** ከሚመሰከሩቸው የቤተ ክርስቲያን አባላት ጋር በመተባበር ትምህርተ ወንጌልን በተለያዩ ዘዴዎች /በመጽሔት፣ በጋዜጣ፣ በካሴትና በበራሪ ጽሑፎች/ ማስፋፋት፣ የተማረው የኅብረተሰብ ክፍል ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያኑን በዕውቀቱ፣ በገንዘቡና በጉልበቱ እንዲያገለግል ትጋት ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና አባላቱ ባላቸው ሙያ፣ ዕውቀትና ገንዘብ ነፃ ሰብአዊ የሆኑ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን እንዲያበረክቱ ማድረግ የሚሉት የማኅበሩ ዓላማዎች ናቸው።

**አስፈላጊነት፡-**

- የተለያዩ የእምነት ድርጅቶች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ እየገቡ ልዩ ልዩ ዘዴ በመጠቀም የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች በአርባና በሰማንያ ቀናቸው ያገኙትን የመንፈስ ቅዱስ ልጅነታቸውን በማሳጣት የራሳቸው ወገኖች ለማድረግ ስለሚሯሯጡ ይህንን የሚገታ ክፍል በየተቋማቱ መገኘት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት እንዲማሩና ከአባቶቻቸው ያገኙትን ትውፊት ለትውልድ ለማስተላለፍ እንዲችሉ አመቺ መንገድ ለመቀየስ፣
- በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በልዩ ልዩ ሙያ ተመርቀው በተለያዩ የሥራ ዘርፎች በልዩ ልዩ የሥራ መስክ የተሰማሩ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በየሄዱበት ቦታ በሚያጋጥማቸው ማኅበራዊ ችግሮች ተውጠው ከቤተ ክርስቲያን እንዳይለዩና ቤተ ክርስቲያናቸውን በጉልበታቸው፣ በገንዘባቸውና በየተማሩበት የዕውቀት ዘርፍ የቤተ ክርስቲያንን ደንብና ሥርዓት ተከትለው እንዲያገለግሉ ለማድረግ፣
- በጥሩ ተምሮ ለሥራ ሲሰማራ እምነቱንና ሥርዓቱን ለመማር እንዲሁም በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤትና ሰበካ ጉባኤ መሳተፍ እንደሚገባው አውቆ በተግባር መተርጎሙን ለመከታተል።

**አቋም፡-** በማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጉዳይም ሆነ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ምንም ዓይነት ጣልቃ ገብነት የለውም።

**አባላት፡-**

- ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ባሏት ማሠልጠኛዎች ሠልጥነው የወጡ በትምህርተ ወንጌል አገልግሎት ላይ የተሰማሩ አባቶችና ወንድሞች ደቀመዛሙርት፣
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አጥቢያ ባሉት የሰንበት ት/ቤቶች መርሐ ግብር የሚማሩ ተማሪዎች፣
- በየአጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶቻቸው መርሐ ግብር ሲከታተሉ ቆይተው ከየተቋማቱ ተመርቀው ከወጡ በኋላ የሰንበት ትምህርት ቤት እና/ወይም የሰበካ ጉባኤ አባል ሆነው መንፈሳዊ አገልግሎት የሚፈጽሙ እና
- ለማኅበሩ ዓላማ ተግባራዊነት በገንዘባቸው በዕውቀታቸውና በጉልበታቸው የሚረዱ ምእመናን ናቸው።

**አባልነት፡-** ከላይ አባላት በሚለው ሥር የተዘረዘሩትን ማሟላታቸው በማኅበሩ መመሪያ መሠረት የተረጋገጠላቸው።

**መዋቅር፡-** በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር ሆኖ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ሲፈጽም በየሀገረ ስብከቱም ንዑሳን ማዕከላት አሉት።

**የአገልግሎት ክፍሎች፡-** የትምህርት ክፍል፣ የመዝሙርና ሥነጥበብ ክፍል፣ የሥልጠና ክፍል፣ የሙያ አገልግሎትና ተራድኦ ክፍል፣ የግንኙነት ክፍል፣ የሒሳብ ክፍል፣ መረጃና መዛግብት ማዕከል፣ የጥናትና ዕቅድ ክፍል፣ የኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል ፣ የልማት ተቋማት አስተዳደር ቦርድ ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org